ጥቅምት 21 2004

# የማንረሳው ወንጀል እና የማንረሳቸው ሰማዕታት

የጥቅምት 22 ሰማዕታትን አስመልክቶ ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ

ጥቅምት 22 1998 ልክ የዛሬ 6 አመት፤ ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ከቤተሰቦቹ በወረሰው የጸረ ኢትዮጵያዊነት ስሜት፤ ፋሽስት ኢጣሊያ በጦር አዝማቿ በግራዚያኒ አማካይነት በአዲስ አበባ ነዋሪዎች ላይ የፈጸመችውን ዓይነት ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ በወገኖቻችን ላይ የፈጸመበት ዕለት ነው።

በበርካታ ምክያቶች የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ዕለት በተለየ ሁኔታ ያስታውሰዋል። ይህ ቀን መለስ ዜናዊ በግንቦት 1997ቱ ምርጫ ከህዝብ የቀማውን የመንግሥት ሥልጣን በሃይል ይዞ ለመቀጠል ወስኖ የንጹሃንን ደም በሃገሪቱ ጎዳናዎች እንደጎርፍ እንዲፈስ ያደረገበት ዕለት ነው። ይህ ቀን የዱር እንስሣት እንኳ በአዳኞች እንዳይገደሉ ዓለም አቀፍ ጥበቃ በሚያገኙበት ዘመናችን፤ ዜጎች በህገ መንግሥት የተደነገገላቸውን መብቶች በሰላማዊ ሰልፍ ስለጠየቁ ብቻ በጠራራ ጸሃይ በአልሞ ተኳሾች ግንባራቸውንና ደረታቸውን በጥይት ተበርጥሰው እንዲገድሉ ትዕዛዝ የተሰጠበት፤ ሺዎች በጥይት የቆሰሉበት፤ ሌሎች ብዙ ሺዎች ከየቤታቸው እየተጎተቱ ተወስደው ከዘረኝነት በሚመነጭ ጭካኔ እየተቀጠቀጡ በቂ መጸዳጃ፣ውሃ፣ ምግብ፣ህክምና በሌለበት እና ዘመድ አዝማድ ወደማይጎበኛቸው እስር ቤቶች የተወረወሩበት ዕለት ነው። ይህ ሁሉ ግፍ የተፈጸመው ወዳጅና ጠላትን ለመለየት በሚመስል ሁኔታ "ህዝብ መሪዎቹን በነጻ እንዲመርጥ" በአዋጅ በተነገረበት ምድር ነው

የጥቅምት 22ን መስዋዕትነት ልዩ የሚያደርገው ሌላው ምክንያት ወያኔ- ኢህአዴግ ባለመታከት ስለራሱ ይደሰኩር ከነበረው የህዝብ ወገንተኛነት በመነጨ ተስፋ ሰማዕታቱ የፍትህ፣ የእኩልነትና የነጻነት ጥያቄ አንግበ ለበትረ ሥልጣን የበቃ ሃይል፤ በጭካኔው ከፋሽስት ኢጣሊያ ጋር የሚመሳሰል ጦር አሰልጥኖና አደራጅቶ ያዘምትብኛል ብሎ ባልጠረጠረበት ወይም ባልጠበቀበት ወቅት የተከፈለ መስዋዕትነት በመሆኑም ጭምር ነው። በዚህም የተነሳ የመለስ ዜናዊን የምርጫ ውጤት ማጭበርበር በሰላማዊ ሰልፍ ለመቃወም አደባባይ የወጣ ብቻ ሳይሆን በየመንደራቸው የጨርቅ ኳስ ይጫወቱ የነበሩ እንቦቅላዎችም ጭምር የጭካኔ ጭፍጨፋው ሰልባ ሆነዋል። በዚያች ታሪካዊዋ ጥቅምት 22 ቀን 1998 ከተጨፈጨፉት 200 በላይ ዜጎች መካከል አብዛኞቹ ገና በለጋ የወጣትነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሲሆኑ ታዳጊ ወጣቶች፤ ሴቶችና አዛውንቶችም ይገኙበታል።

የጥቅምት 22 1998 ሰማዕታት ጥያቄ፤ በመልካም አስተዳደር ጉድለት ለዘመናት በአገራችን ምድር ተንሰራፋቶ የኖረው ኢፍትሃዊነት፣ ድህነትና ኋላ ቀርነት ይወገድ ዘንድ ህዝብ በታሪኩ ለመጀመሪያ

ጊዜ በነቂስ ወጥቶ ያስተዳድሩኛል ብሎ የመረጣቸው ተወካዮቹ ተገቢውን የሥልጣን ቦታቸውን እንዲይዙና ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረታዊ የሆኑ ነጻ መንግሥታዊ ተቋማት እንዲመሰረቱ ብቻ ነበር ።

በወቅቱ በጅምላ ወደ እስር ቤት የተወረወሩት የቅንጅት መሪዎችም ቢሆኑ ጥያቄያቸው መለስ ዜናዊና ፓርቲው እንደተሸነፈ እያወቁ "ትንሽ መብቶችን ስጠንና ለሌላ 5 አመት ተጨማሪ ጊዜ ግዛን " የሚል ነበር።

ሆኖም ግን በጸረ ኢትዮጵያ ስሜት ተጸንሶ ለተወለደው መለስ ዜናዊና ስልጣንን መከታ በማድረግ በዘረፉ በተገኘው ሃብት ሂሊናቸው ለደነዘዘው ጥቂት ግብረአበሮቹ፤ በአገርና በህዝብ ኪሳራ ስልጣንን እስከወዲያኛው ማራዘም ቀዳሚነት ያለው ሆነና ያ ሁሉ ዘግናኝ ግፍ በወገኖቻችን ላይ ተፈጸመ።

በዚህም የተነሳ የመከራና የጭንቅ፤ የጦርነትና የረሃብ አስከፊ ታሪካችንን ወደኋላ ትተን በአገራችን ሠላማዊና ዲሞክራሲያዊ የሆነ የስልጣን ሽግግር በማምጣት ሁላችንም ያለንን ጉልበት፤ ዕውቀትና ገንዘብ በማንቀሳቀስ ፈጣን ወደ ሆነ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጎዳና እንገሰግሳለን ብለን የሰነግነው ራዕይና ተስፋ ለጊዜውም ቢሆን ተሰናከለ። በአንጻሩም መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ ወደድንም ጠላን እስከወዲያኛው ረግጠው እንዳሻቸው ሊገዙን እንደሚችሉ አረጋገጡ።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህንን የዘንድሮውን 6ኛ አመት የጥቅምት 22 ሰማዕታት ቀን የሚዘክረው፤ ሰማዕታቱ ህይወታቸውን የተሰውለትን መልካም አስተዳደር በአገራችን ለማስፈን ይቻል ዘንድ ለፍትህ፣ ለእኩልነትና ለነጻነት የሚደረገውን ትግል ከዳር ለማድረስ ያለውን ቁርጠኝነት እንደገና በማደስ፤ የአጋዚን ጦር አሰልጥኖና አስታጥቆ በወገኖቻችን ላይ ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዲፈጽም ግልጽ ትዕዛዝ የሰጠውን መለስ ዜናዊንና ጥቂት ግብረአበሮቹን በተባበረ ትግል ህግ ፊት ለማቅረብ ትግሉ የሚጠይቀውን ማንኛውንም ዓይነት መሰዋዕትነት ለመክፈል ቁርጠኝነቱንና ዝግጁነቱን በመግለጽ ነው።

በዚህ አጋጣሚ፤ በአረመኔያዊ የመለስ ዜናዊ ጨካኝ ጭፍጨፋ ምክንያት ልጆቻቸውን፣ ባሎቻቸውን፣ሚስቶቻቸውን፣ ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን በአጋዚ ጥይት ለተነጠቁት ሁሉ ሃዘናችሁ ሃዘናችን መሆኑን ደጋግሞ እየገለጸ የፈሰሰው የወገኖቻችን ደም በከንቱ እንደማይቀር ቃል በመግባት ነው።

ገዳዮችን ለፍርድ እስክናቀርብ ድረስ ቀበቶአችንን አናላላም!!!

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!